| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ጽሑፍ ፤ "አኃዛውያን ፡ ልቅሞች ።" |
| ርእስ ፤ | "የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ወቅት ፥ የሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ ፡ አባላት ፡ ምጣኔ ፥ በክፍላተ ፡ ሀገሩ ፡ ነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ መሠረት ።" |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ሚያዝያ ፡ 2015 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2015-002 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | (ስሕተቶች ፡ በተገኙ ፡ ወይ ፡ በተጠቈሙ ፡ ቍጥር ፡ ታርመው ፥ ዝርዝራቸው ፡ ዳግመኛ ፡ ይወጣል ። ) |

# የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ወቅት ፥ የሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ ፡ አባላት ፡ ምጣኔ ፥ በክፍላተ ፡ ሀገሩ ፡ ነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ መሠረት ።

የእያንዳንዱን ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ የነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ በተመለከተ ፥ ከደርግ ፡ ዘመን ፡ አንሥቶ ፥ ባለፉት ፡ 50 ፡ ዓመታት ፡ በኢትዮጵያ ፡ **ማእከላዊ ፡ የአኃዝ ፡ ምድራግ** ፡ (Central Statistical Agency) ፡ የተሰናዱት ፡ አኃዞች ፥ **በኢትዮጵያ** ፡ የ"አፓርትሀይድ" ፡ ሥርዐትን ፡ ለመትከል ፡ እንዲያመች ፥ በእየጊዜው ፡ የተነካኩ ፡ እና ፡ የተበጃጁ ፡ በመኾናቸው ፡ ይህ ፡ ጥናት ፡ አስወግዷቸዋል ። በምትካቸው ፥ ከምንም ፡ ዐይነት ፡ ፀረ-ሀገር ፡ ዐላማ ፡ በጸዳ ፡ መንፈስ ፥ በ 1938 ፡ ዓ.ም. (+) ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ መንግሥት ፡ በሀገር ፡ ግዛት ፡ ምጋቤ ፡ የተካኼደውን ፡ ሀገራዊ ፡ የነዋሪዎች ፡ ቈጠራ ፡ መነሻ ፡ አድርጓል ።

ባለፉት ፡ 77 ፡ ዓመታት ፡ በታዩት ፡ የነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ እድገት ፡ ረገድ ፥ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ምንጮች ፡ የተገኙትንም ፡ መረጃዎች ፡ በማጠናቀር ፥ ለ 2015 ፡ ዓ.ም. ፥ በእየክፍለ ፡ ሀገሮቹ ፡ አንጻር ፡ የተገመቱትን ፡ አኃዞች ፡ በሰንጠረዥ ፡ መልክ ፡ እንደሚከተለው ፡ አቅርበናል ። *(የጥናቱን ፡ ሙሉ ፡ ዝርዝር ፡ ከ"ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፡ ማግኘት ፡ ይቻላል ። )*

ማንኛውንም ፡ አስተያየት ፣ ዕርማት ፣ ምክር ፣ ወዘተርፈ ፡ ሊለግሱን ፡ የሚሹ ፡ ኹሉ ፥ በእ-ጦማር ፡ አድራሻችን ፡ በ ፦

sh1@ttomar.net

ሊያደርሱልን ፡ እንደሚችሉ ፡ ባክብሮት ፡ እናስታውቃለን ።

## የሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ ፡ አባላት ፡ ክፍለ ፡ ሀገራዊ ፡ ምጣኔ ፤

| ክፍለ ፡ ሀገር | የነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ በ 2015 ፡ ዓ.ም. (በሚልዮን) | (በ%) | የተወካዮች ፡ ብዛት ፡ (1 ፡ ተወካይ ፡ ለ 200'000 ፡ ነዋሪዎች) | (ድማሪ) |
|---|---|---|---|---|
| ሸዋ | 16.7 | 13.8 % | 84 | (84) |
| ጐዣም | 13.4 | 11.0 % | 67 | (151) |
| ወሎ | 12.8 | 10.5 % | 64 | (215) |
| ጐንደር | 12.2 | 10.0 % | 61 | (276) |
| መናገሻ | 8.5 | 7.0 % | 43 | (319) |
| ሲዳሞ | 8.3 | 6.8 % | 42 | (361) |
| ትግራይ | 7.8 | 6.4 % | 39 | (400) |
| ሐረርጌ | 7.2 | 5.9 % | 36 | (436) |
| ጋሞ ፡ ጎፋ | 6.7 | 5.5 % | 34 | (470) |
| ከፋ | 6.7 | 5.5 % | 34 | (504) |
| ዐሩሲ | 5.6 | 4.6 % | 28 | (532) |
| ወለጋ | 4.5 | 3.7 % | 23 | (555) |
| ኢሉባቦር | 3.9 | 3.2 % | 20 | (575) |
| ባሌ | 3.9 | 3.2 % | 20 | (595) |
| ኤርትራ | 3.2 | 2.6 % | 16 | (611) |
| ኢትዮጵያ | 121.4 | 100.00% | 611 | |

(+) ኤርትራን ፡ እና ፡ የኦጋዴን ፡ አውራጃን ፡ ሳይጨምር ፥ በቀሩት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍሎች ፡ በ 1938 ፡ ዓ.ም. ፡ በተደረገው ፡ የነዋሪዎች ፡ ቈጠራ ፡ መሠረት ፥ የተገኘው ፡ ግምት ፡ 30 ፡ ሚልዮን ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፥ ካ 12 ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፥ በ 1950 ፡ ዓ.ም. ፥ ለተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ የተላለፈው ፡ አኃዝ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ትእዛዝ ፡ በ 8 ፡ ሚልዮን ፡ ተቀንሶ ፥ 22 ፡ ሚልዮን ፡ ተብሎ ፡ ነበር ። ይህን ፡ ለመወሰን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ምን ፡ እንዳስገደዳቸው ፡ በትኽክል ፡ ባይታወቅም ፥ በወቅቱ ፡ የተሰጠው ፡ ምክንያት ፦ *ኢትዮጵያ ፡ ለተ.መ.ድ. ፡ በእየዓመቱ ፡ የምታገባው ፡ መዋጮ ፡ በነዋሪዎቿ ፡ መጠን ፡ ስለሚሰላ ፥ የመዋጮውን ፡ መጠን ፡ ለመቀነስ ፡ ታስቦ ፡ ነው ፡ የሚል* ፡ ነበር ። የኾነው ፡ ኾኖ ፥ ይህ ፡ ዝቅተኛ ፡ መነሻ ፥ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ "ፍድፋዴ" ፡ መግታትን ፡ ለሚሹ ፡ የውጭ ፡ ኀይሎች ፥ በእየጊዜው ፡ የሚመነደግ ፡ አኃዝን ፡ በመልቀቅ ፥ የወሊድ ፡ መቈጣጠሪያ ፡ ሥራዎችን ፡ በሰፊው ፡ ለማስፈጸም ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ኾኗቸዋል ። በመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ወቅት ፥ ከዋነኛዎቹ ፡ ሥራዎች ፡ አንዱ ፥ የኢትዮጵያን ፡ ***ማእከላዊ ፡ የአኃዝ ፡ ምድራግ*** ፡ *(Central Statistical Agency)* ፡ ሥራ ፡ ማስመርመር ፡ ይኾናል ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2015 ፡ ዓ.ም. ።

# የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ወቅት ፥ የሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ ፡ አባላት ፡ ምጣኔ ፥ በክፍላተ ፡ ሀገሩ ፡ ነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ መሠረት ።

(የነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ ግምት ፡ ከ 2015 ፡ ዓ.ም. ፥ በ 1962 ፡ ዓ.ም.ቱ ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ አከፋፈል ፡ መሠረት ። )

| ክፍለ ፡ ሀገር | ቢጋር | የነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ (በሚሊዮን) ከ 2015 ፡ ዓ.ም. | የተወካዮች ፡ ብዛት ፡ (በ 1 ፡ ተወካይ ፡ ከ 200'000 ፡ ነዋሪዎች ፡ ሒሳብ) |
|---|---|---|---|
| መናገሻ ፡ አውራጃ (ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ) |  | 8.5 ፡ ሚሊዮን ፡ ነዋሪዎች (6.3[1] ፡ ሚ.) | 43 ፡ ተወካዮች (32 ፡ ተወካዮች) |
| ሸዋ |  | 16.7 ፡ ሚሊዮን ፡ ነዋሪዎች (25.2 ፡ ሚሊዮን ፥ የመናገሻ ፡ አውራጃን ፡ 8.5 ፡ ሚሊዮን ፡ ነዋሪዎች ፡ ጨምሮ) | 84 ፡ ተወካዮች |
| ጎጃም |  | 13.4 ፡ ሚሊዮን ፡ ነዋሪዎች | 67 ፡ ተወካዮች |
| ወሎ |  | 12.8 ፡ ሚሊዮን ፡ ነዋሪዎች | 64 ፡ ተወካዮች |
| ስሜን ፡ እና ፡ በጌምድር |  | 12.2 ፡ ሚሊዮን ፡ ነዋሪዎች | 61 ፡ ተወካዮች |
| ሲዳሞ |  | 8.3 ፡ ሚሊዮን ፡ ነዋሪዎች | 42 ፡ ተወካዮች |
| ትግራይ |  | 7.8 ፡ ሚሊዮን ፡ ነዋሪዎች | 39 ፡ ተወካዮች |
| ሐረርጌ |  | 7.2 ፡ ሚሊዮን ፡ ነዋሪዎች | 36 ፡ ተወካዮች |
| ጋሞ ፡ ጎፋ |  | 6.7 ፡ ሚሊዮን ፡ ነዋሪዎች | 34 ፡ ተወካዮች |

1 የዐዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ የነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ ባማካይ ፡ በዓመት ፡ 2.8% ፡ እያደገ ፥ በ 64 ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ በ 1948 ፡ ዓ.ም. ፡ ከነበረበት ፡ 1 ፡ ሚልዮን ፥ በ 2015 ፡ ዓ.ም. ፡ 6.3 ፡ ሚልዮን ፡ ደርሷል ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ። ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ የሚገኝበት ፡ የመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ ነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ እድገት ፡ ግን ፡ በዚያው ፡ በ 1.18% ፡ አማካይ ፡ ሀገራዊ ፡ ዓመታዊ ፡ የነዋሪዎች ፡ እድገት ፡ መጠን ፡ ተሰልቷል ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2015 ፡ ዓ.ም. ።

| ክፍለ ፡ ሀገር | ቢጋር | የነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ (በሚልዮን) ከ 2015 ፡ ዓ.ም. | የተወካዮች ፡ ብዛት ፡ (በ1 ፡ ተወካይ ፡ ከ 200'000 ፡ ነዋሪዎች ፡ ሒሳብ) |
|---|---|---|---|
| ከፋ |  | 6.7 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች | 34 ፡ ተወካዮች |
| ዐሩሲ ፡ (ዐርሲ) |  | 5.6 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች | 28 ፡ ተወካዮች |
| ወለጋ |  | 4.5 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች | 23 ፡ ተወካዮች |
| ኢሉባቦር |  | 3.9 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች | 20 ፡ ተወካዮች |
| ባሌ |  | 3.9 ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች | 20 ፡ ተወካዮች |
| ኤርትራ (ባሕር ፡ ምድር ፡ እና ፡ ደንከል) |  | 3.2 [2] ፡ ሚልዮን ፡ ነዋሪዎች | 16 ፡ ተወካዮች |
| ኢትዮጵያ |  | 121.4 ፡ ሚልዮን [3] ፡ ነዋሪዎች | በድምሩ ፡ 611 ፡ ተወካዮች ፡፡ |

2 የክፍለ ፡ ሀገር ፡ ኤርትራ ፡ ነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ በ 1938 ፡ ዓ.ም. ፡ ከነበረበት ፡ 1 ፡ ሚልዮን ፡ በ 2015 ፡ ዓ.ም. ፡ 4 ፡ ሚልዮን ፡ መድረስ ፡ ነበረበት ፡፡ ነገር ፡ ግን ፥ ባለፉት ፡ 50 ፡ ዓመታት ፡ በክፍለ ፡ ሀገሩ ፡ የደረሰው ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነት ፡ ባስከተለው ፡ ነውጥ ፥ ካ 1 ፡ ሚልዮን ፡ ያላነሱ ፡ ነዋሪዎች ፡ ወደስደት ፡ ዓለም ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሌሎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍሎች ፡ በመፍለሳቸው ፡ ምክንያት ፥ በ 2015 ፡ ዓ.ም. ፥ የክፍለ ፡ ሀገሩ ፡ የነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ ከ 3.2 ፡ ሚልዮን ፡ እንደማይበልጥ ፡ ይገመታል ፡፡

3 እውጭ ፡ ሀገር ፡ የሚኖሩ ፡ 3.3 ፡ ሚልዮን ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ሳይጨምር ፥ በ 2015 ፡ ዓ.ም. ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፡ ነዋሪዎች ፡ ብዛት ፡ (1.1 ፡ ሚልዮን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጎችን ፡ ጨምሮ) ፡ 122.5 ፡ ሚልዮን ፡ ይገመታል ፡፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2015 ፡ ዓ.ም. ፡፡